የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)

# SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

**ኅዳር** 17/2002

## <u>በሴቶች ላይ የሚደርሰው በደል ያብቃ!</u>

***በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጨመረ የመጣውን ሴቶችን የመደብደብና የማጥቃት ልምድ ለመቃወም የተደረገውን ጥሪና ዘመቻ ኢፖእአኮ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ በሀገር ቤትና በባዕድ ሀገርም እየደረሰ ያለውን ድብደባና ስቃይ በጥብቅ ያወግዛል። ሁሉም ዜጋ ይህን መብት ረጋጭና ኢሰብዓዊ ድርጊትና ልምድ እንዲቃወምም ጥሪውን ያስተላልፋል።***

***በዘልማድ ሴቶችን የመደብደብ ድርጊት በሀገራችን በሰፊው ሲፈፀም የቆየ ሲሆን ዛሬም በሰፊው መቀጠሉን የምናውቀው ነው። ሴትና ..... ካልተደበደበ .... ወዘተ የሚሉ ኋላቀር አባባሎች ዛሬም አልተረሱም። የማይወራና የሚድበሰበስ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ብዙ ሚስቶች በባሎቻቸው ይደበደባሉ። ህፃናት ሴቶችም እንዲሁ የድብደባ ሰለባ ናቸው። ለዘመናዊ ባርነት ወደ ባዕድ ሀገሮች በተለይም ወደ መካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች የተላኩ ወጣት ሴቶችም ብዙ ድብደባና ሁለገብ በደል ይደርስባቸዋል፣ ሴቶችን የመድፈር ወንጀልም መቀነስ ሳይሆን እየበዛ ነው። ያለው ስርዓት የሞራል ድቀትና የስነ ምግባርን ዝቅጠት በማስፋፋቱ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶች በዘመድ ሳይቀር በብዛት እየተደፈሩ መሆናቸው በየጊዜው እየተዘገበ ነው። ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ የተዳሩና ጤናቸውም ኑሮአቸውም የተበላሸ ብዙ ሺ ለጋ ዜጎች የዚሁ አሰቃቂ በደል ሰለባ ናቸው።***

***የሴቶች መደፈርን የሚቀጣ ህግ ተፅፎ ቢገኝም በስራ ካለመዋሉ ሌላ ሴቶች ላይ በደል በማድረሱየገዢው ቡድን አባላት ቀዳሚዎች መሆናቸውም የሚካድ አይደለም። ፍትሕ ወንድ ናት የሚባለው እንዲሁአይደለም። በዋና መልኩ ተተኩሮበት በሰሞኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘመተበት ሴቶችን በቤት ውስጥ የመደብደቡ ጉዳይ ግን ሾላ በድፍን ወይም የሚደበቅ ገበና ሆኖ መታለፍ የሌለበት ነው።ሴቶችንመደብደብና ማሰቃየት መወገዝ ያለበት መብት ረገጣ ነዉ። ባሎች በሚስቶቻቸው ላይ የመደብደብ መብት የላቸውም። ግለሰቡን/ደብዳቢውንና ህብረተሰባችንንም የሚያስገምት ድርጊት ነውናኢፖእአኮ ለሰብዓዊ መብት መከበር ተሟጋች እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ድብደባና ሁሉንም ዓይነት በደል በጥብቅ ይቃወማል። ወንዶችም ከዚህ ኋላቀር ድርጊትእንዲርቁ ጥሪውን ያስተላልፋል። ሴቶችም ለመብታቸው ለመታገል እንዲደራጁና ትግላቸውን ም እንዲያስተባብሩ ያሳስባል።***


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE